# አንቺው ታመጪው…እንዲሉ ካመጣሽውማ

## ከመድረኩ ደርግ ይሻላል!!

## ክፍል አንድ

**ዮናስ 12-11-14**

በኢትዮጵያ የፖለቲካ የትግል ታሪክ ውስጥ ሃገሪቱን ለ17 ዓመታት በድህነትና በአምባ ገነናዊ ሥርዓቱ ቀፍድዶ የገዛትና እልፍ አእላፎችን ለእልቂት የዳረገው ደርግ በምንም መለኪያ ከየትኛውም አካል (ፖለቲካዊ ድርጅት.ጋር) ሊነጻጸር አይችልም፡፡ ያም ሆኖ ግን በጋዜጠኝነት ቆብ ሲንቀሳቀስ የነበረውና በኋላም ከአሸባሪ ድርጅቶች ጋር ሲሰራና ህገመንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ ሲያሴሩ ከነበሩ ሃይሎች ጋር ሲያሴር የነበረ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ የቅጣት ውሳኔ የተላለፈበት ተመስገን ደሳለኝና መሰሎቹ ደርግን ከገዢ ሥርዓቱ ጋር ማነጻጸር በጀመሩበት አግባብ፣ የወቅቱ የመድረክ የውጭ ግንኙነት ሃላፊና ጽንፈኛ ብሄርተኛ መሆናቸው በተለያዩ አግባቦች የሚረጋገጠው ዶ/ር መራራ ጉዲና ‹‹ከኦሮሚያ አንጻር ከኢህአዴግ ደርግ ይሻላል›› ሲሉ አንድ ትርክት ከሰሞኑ ማስነበባቸው ነው የዚህ ጸሁፍ መነሻ፡፡

እርሳቸው ስላመጡትና ባልደረቦቻቸው ስላሮጡት እንጂ ደርግን በራሱ የሚሻልባቸው አጋጣሚዎች እንኳ ቢኖሩ ሚዛን ላይ አስቀምጦ ለማንጸር የሞራልም ሆነ የፖለቲካ ተጠየቆች የማይፈቅዱ ከመሆኑ አንጻር ለውድድር ማብቃቱ ተገቢ አልነበረም፡፡ ይሁንና ተገቢ ያልሆናበቸውን ምክንያቶች ይዘን ግን ካመጡት ዘንዳ ደርጉ ከመድረኩ የሚሻልበትን ሁኔታዎች በተለይም ከኢትዮጵያችን ተጨባጭ ሁኔታዎች አንጻር ማስቀመጥ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

ዶ/ር መራራ በሠንደቅ ጋዜጣ ቁጥር 482 ህዳር 24/2007 የደርጉን ከኢህአዴግ መሻል ያጠየቁባቸውን ምክንያቶች እንደወረዱ ከማሄሳችን በፊት ደግሞ መድረኩንና የመድረኩን በተለያዩ የሥልጣን አይነቶች ደረስ መለስ እያሉ ከሚያዘወትሩቱ ዶ/ር መራራና ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ አኳያ እናሄሳለን።ከማሄሳችን በፊት ግን ስለራሳችን ትክክለኝነት የመድረኩን ከደርግ የባሱ ክፋቶች ማረጋገጥ እንዲቻለን ወደኋላ መለስ ብለን ምርጫ 97 እና ምርጫ 2002ን ከነዚሁ ግለሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶቻቸው አንጻር በትዝታ ማስታወስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በሃገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተወገደውን የደርግ ሥርዓት ተከትሎ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገው ርብርብ በየደረጃው የቀጠለ ቢሆንም፤ የዴሞክራሲ ተቋሟት የሚባሉቱ ድርጅቶችም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ከእለት እለት እየተጠናከሩና የበለጠውኑ እየሠሩ ያሉበት ሁኔታ ቢኖርም፤ በሃገራችን የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሚዲያው በተለይም ምርጫ በደረሰ ቁጥር ልክ እንደመሥቀል ወፍ የተለመደና ጸረ ዴሞክራሣያዊ የሆነ አካሄዳቸውን ለማለዘብና ወደትክክለኛውና ለሃገራችን እድገት ወደሚጠቅመው መሥመር መመለሥ አለመቻላቸው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው ላይ ከባድ የተባለ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳረፈ ነው፡፡

በተለይም እንደ ገዢው ፓርቲ የተቃዋሚዎቹ ጎራ እና ከነዚሁ ጎን የተሰለፉቱ ፕሬሶች በምርጫ 97 ያሳዩት የፖለቲካ ውሥልትና ጎልቶ የተሥተዋለው ከምርጫው በኋላ እንደሆነ ሲወሳ በምርጫ 2002 ደግሞ የአመፅን መንገድ የጀመሩት ገና ከዋዜማው እንደሆነም ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም ድህረ ምርጫ 97ን እና ቅድመ ምርጫ 2002ን በጥቂቱ በማንሳት አሁን ደግሞ በምርጫ 2007 ዋዜማ ላይ ያለውን የህዳሴ ጉዞ ከተቃዋሚዎቹ ውዝግብ አኳያ እንመለከታለን፡፡

በሦሥተኛው አገራዊ ምርጫ ፉክክሩ፣የድምፅ መሥጠትና የቆጠራ ሂደት ሁሉም በሠላም መጠናቀቁን ተከትሎ አሸናፊው ወገን ቢለይም ተቃዋሚው ሃይል በተለይም ቅንጅትና ህብረት አሁን ደግሞ መድረክ በሚባለው ፓርቲ ሥር የተጠለሉቱ ሃይሎች ውጤቱን በፀጋ ለመቀበል አልፈቀዱም፡፡

ውጤቱን በተመለከተ ሃላፊነትና ሥልጣን የተሰጠው አካል ባደረገው የማጣራት ስራ (በገዢውም ሆነ በተቃዋሚው በኩል የቀረቡ ታዛቢዎችን በማካተት) የተቃዋሚዎቹ የአሸንፈናል አዋጅ ተገቢነት እንደሌለውና ጥቂት በሚባሉ ቦታዎች ላይ ደግሞ ምርጫ እንዲደገም በመወሰኑ ቀድሞውኑም ቢሆን በአቋራጭ ሥልጣን የቋመጠው ሃይል ለህግ አልገዛም ባይነቱን ቀጠለበት፡፡

እነዚህ አሁን በመድረክ ጥላ ሥር የሚገኙትና በ3ኛው ምርጫ ክፍለ ጊዜ በቅንጅትና በህብረት ሥር የነበሩት ሃይሎች በወቅቱ በያዙት የዜሮ ድምር ፖለቲካ ቀጥለው አመፅ

በመቀስቀስ ወደሥልጣን ለመምጣት ያላቸውን ውጥን እውን ለማድረግ፣ በቀን ቢያንሥ ከሦሥት ጊዜ በላይ የፕሬስ መግለጫ በመስጠት አመፁን ለማጋጋል ያላሰለሰ ጥረት ማድረጋቸውን አንዘነጋም ፡፡

ይህንኑም የወቅቱ የኢህአዴግ የምርጫ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡፡ "አብዶ ማሳበድ የሚያውቀው የኢትዮጵያ የግል ፕሬስ የቅንጅትን የጢትና ማታ መግለጫዎች በሰፊው ያራግባል፡፡"

ከዚህ በመነሳት የግል ፕሬሱና ተቃዋሚው ድህረ ምርጫ 97 ከህግ የበላይነት በላይ በመሆን ህግንና ህገወጥነትን በማጣቀስ የተቋማትን ህጋዊና ሉአላዊ ስልጣን ከመጋፋት ጀምሮ ገዢው ፓርቲንም ሆነ መንግሥት አልፎም የባለሥልጣናትን የግል ጉዳይ ሳይቀር በማንሳትና ጮሀው በማጯጯህ ሃገሪቷን ለትርምስና ወንበሩን ለራሳቸው ቢመኙም በአለም አቀፍ ደረጃ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ ወደጎን ተገፍቶ የሰለጠነ የውይይትና የድርድር ባህል ወሳኝ ቦታ እየያዘ መምጣቱን በተገነዘበው ህዝብና ባስገነዘበው መንግሥት፣ የጥላቻና የአመፅ ፖለቲካ፣ ምርጫን የአመፅ መሳሪያ ማድረግና በምርጫ ሰበብ ሁከት መቀስቀስ ፀረዴሞክራሲያዊነትና ዘመን ያለፈበት ፈሊጥ መሆኑን በተገነዘበው ህዝብ አማካኝነት ምኞታቸው ሁሉ ከሽፎ ጉዞ ወደ ቃሊቲና ወደ ህዳሴ ሆነ፡፡

የነውጠኛው አመራር በይቅርታ ከተፈታ በኋላ ገሚሱ በይፋ የአሸባሪ ቡድን አደራጅቶ ስንቀሳቀስ ገሚሱ ደግሞ ላመለጠችው ወንበርማ ዋንጫ እንደገና ለመፋለም ግንባር ፈጥሮ መድረክ በሚል መለያ ቢንቀሳቀስም ነገሩ ያደቆነ ሰይጣን ሆነና አሁንም እንደገና ህገወጥነትን እያጣቀሱ መቀጠልንና ምርጫውን ገና ከዋዜማው ማጠልሸት ጀመሩ፡፡ በዚሁ የውግዘትና የአመጽ ፓለቲካ በቅንጅት ዶቅነው በመድረክ የቀሰሱት ሃይሎች የምርጫ 2002 የመራጮች ምዝገባና ቅስቀሳ ሳይጀምር "ካሸነፍን ትክክል ነው ከተሸነፍን ግን ተጭበርብሯል" የሚል ፊሽካቸውን ነፉ፡፡

የዜሮ ድምር ስብሰቡ ከላይ በተገለፀው መልክ ምርጫ 97 ላይ በዜሮ ቢሸነፍም በተለይም የስብሰቡ አደራጅ የሆኑት አንዳንድ አለም አቀፍ ድርጅቶችና በነፃ ፕሬስ ስም የተቋቋሙ ሃገር በቀል ጋዜጦች ከምርጫ 2002 ወደኋላ 2 ዓመት ቀደም ብለው መድረክ የተባለ ጠንካራና የብዙ ፓርቲዎች ጥምረት የሆነ ፓርቲ መወለዱን በይፋ ማወጅና ማራገብ ቢጀምሩም መድረክ የተባለው ፓርቲ ከወዴት እንዳለና አመጣጡም ከወዴት እንደሆነ

ሳይታወቅ ቢቆይም  በምርጫ 2002 ዋዜማ ላይ የተለመደውንና በምርጫ 97 በዜሮ የተሸነፈበትን የቅንጅት አጀንዳ ይዞ ብቅ አለ፡፡

ሆኖም ይህ ፓርቲና ስብስቡ ልክ እንደ ምርጫ 97ቱ ቅንጅት ቅጥ አምባሩ የጠፋና የሚያስተሳስርና አንድ የሚያደርገው ቀጭን ገመድ እንኳ የሌለው መሆኑ ገና ከመነሻው ግልፅ ነበር፡፡ ይህንንም አቶ በረከት በሁለት ምርጫ ወጋቸው ላይ እንዲህ ይገልፁታል” አንዱ ሶሻል ዴሞክራቲት ነኝ ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ ሊበራል ዲሞክራት ነኝ ይላል፡፡ አንዱ የኦሮሞ ህዝብ በቁመቱና በወርዱ ልክ መብቱ አልተከበረለትም ይላል፡፡ ሌላው ኢህአዴግ የሚባል ድርጅት ለብሔር ብሔረሰቦች ከልክ በላይ መብት ሰጥቶ አገሪቱን ሊያፈራርሳት ነው ይላል፡፡አንዱ የሚናገረውን ሌላው ያፈርሰዋል፡፡ ደግሞ እንደገና ሌላው ያፈረሰውን አንዱ ሊገነባ ይውተረተራል፡፡ ከኦሮሚያ ፌልቀናል የሚሉት ዶ/ር መራራ፡አቶ ቡልቻና ዶ/ር ነጋሶ የሶስት የተለያዩ ደርጅቶች ባለቤት ሆነው ስለመድረክ ጥንካሬ ያወራሉ፡፡ - - -“

ስለሆነም ይህ ሁኔታ በመንግስትና በህዝብ ቁርጠኝነት በቁጥጥር ስር የዋለውን የድህረ ምርጫ 97 አመፅ ለመድገም የተደረገ ሴራ መሆኑን መንግሥት በመገንዘብና እነሱም በዛ ወቅት የጠፋው ሰውና ንብረት መጥፋት የሌለበት መሆኑን በመገንዘብ የጋራና ሁሉንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊያግባባ የሚችል የፓለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ማዘጋጀት እንዳለበት በኢህአዴህ በኩል ጥሪ የቀረበ ሲሆን እንደተፈራውም ሌሎቹ ፓርቲዎች አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እና የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች በማገናዘብ የስነምግባር ደንብና የምርጫ ስነምግባር ማዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ በማመን ወደድርድሩ ገብተው የተስማሙበትን ሰነድ አዘጋጅተው በማፅደቅ ወደሥራ ቢገቡበትም መድረክ የተባለው ፓርቲ ውልደቱ ከቅንጅት በመሆኑ እምቢኝ ባይነቱን ገፋበት፡፡

አንዳሰበውም ምርጫው ገና ሳይደረግ "ተጭበርብሯል" ከማለቱም ባሻገር በምርጫው ተሳትፎ ገና ድምፅ የመስጠቱ ሂደት ሳይጋመስ በቀትር ሰዓት ላይ አንዳቸው ተጭበርብራል  ሲሉ ሌላኛቸው ደግሞ የአሸንፈናል አዋጅ አስነገሩ፡፡

የሆነ ሆኖ አሁንም መነሻቸው የዜሮ ነበርና ከፍልሚያው በዝረራ ቢወገዱም አሁንም ለቀጣዩ ምርጫ ቅጣምባራቸው የጠፋባቸውና ምንም የውልና የትስስር መስመር የሌላቸው

ፓርቲዎችን በመሰብሰብ ከወዲሁ እና ከዋዜማው ቀጣዩ ምርጫ የሁከትና የትርምስ ይሆን ዘንድ በመልፋት ላይ ይገኛሉ፡፡

በቀጣዩ ግንቦት ወር የሚካሄደውን ሃገር አቀፍ ምርጫ በተመለከተ መድረክ የተባለውና በሥሩ ያሰባሰባቸው ቡድኖች የሚያነሱትን ጥያቄ በ2002 በፓርቲዎች ም/ቤት ፀድቆ በሥራ ላይ የዋለው የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባርና ደንብ ቁልጭ አድረጎ የመለሰ ሲሆን ይህንኑ ጥያቄ በተገቢው መንገድ ይፈታ ዘንድና በምርጫው ከመፋለም ባሻገር ያሉ የሚዲያ የፋይናንስና ሌሎች ጥያቄዎች ለመመለስ ጉዳዩ የኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የጋራ ፓርቲዎች ምክር ቤቱ አካል የመሆንንና በሰነዱ ላይ ተስማምቶ መፈረምን መጀመሪያ የሚጠይቅ እንደሆነ ሰነዱ በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑና አሁንም የጋራ ም/ቤቱ አካል መሆን እንደሚቻል የሰፈረ በመሆኑ በዚሁ መሰረት መድረክ የተባለውና ጥያቄ አለን የሚሉት ፓርቲዎች መንቀሳቀሥ ሲጠበቅባቸው አሁንም ጊዜ ላለፉበት ፖለቲካ ተገዢ በመሆን የተናጥል ድርድር በመጠየቅ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ለሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፋይዳ የሌለው ተራ የፖለቲካ ቁማር ነው፡፡ ተመሳሳይነቱና መድረክ የተባለው ፓርቲ የአቋራጭ ስልጣን ፈላጊ መሆኑን የሚያሳብቀው አሁንም በየጊዜውና ምርጫ በደረሰ ቁጥር የፖለቲካ አማራጮች ከማቅረብ ባሻገር በተምታቱ መግለጫዎች የተጥለቀለቀ መሆኑና ይህንኑም የነፃውን ፕሬስ ታፔላ የለጠፉ ጋዜጦች ማራገባቸውን አጠናክረው የቀጠሉበት መሆኑ ነው፡

በመግቢያዬ አካባቢ እንደጠቆምኩት ዶ/ር መራራ የሞቱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆናቸውንና ስርዓቱ እንዳለ መሆኑን እያወቁት ስርዓትን ለመለወጥ ደግሞ ምርጫ የግድ ስለመሆኑና ሃገር አቀፍ ምርጫው ገና 2 ዓመት እነደሚቀረው እየታወቀ በአናቱም የፖለቲካል ሳይንስ ዱክትርና እላቸው ያኔም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያልፉ የፖለቲካና የስርአት ለውጥ ማሰባቸው ቂልነታቸውን ሳይሆን የአቋራጭ ወንበር ፈላጊ መሆናቸውንና የበርጬማ ፖለቲካ አቀንቃኝ መሆናቸውን የሚያመላክት ነው፡፡

በአጠቃላይ በዳበረ የዴሞክታሲ ስርዓት ገዥ የነበረ ፓርቲ ተቃዋሚ ተቃዋሚ የነበረውም ገዢ የመሆኑ ጉዳይ የተለመደና የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ እንደዚህ አይነት የስልጣን ሽግግር ያለአንዳች ችግርና ቀውስ በሰላማዊ መንገድ የሚፈፀም ከመሆኑም ባሻገር ህብረተሰቡ

በሚመራባቸው መሰረታዊ አቅጣጫዎች ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥን የሚያስከትል አይሆንም፡፡

ይህ የሚሆነው ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ታማኝ ተቃዋሚ(ሎያል ኦፖዝሽን) በሚል ስያሜ የሚታወቁ የራሳቸው የተለየ ፓሊሲ ከማቅረብ ባሻገር ስርዓቱን የመናድ ሃሳብና ተግባር የሌላቸው ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ እንደነ ዶ/ር መራራ ጉዲና በህግ የሚመሩትንና ህገመንግሥታዊ ስርዓቱን አክብረው በተፈቀደው ሜዳ ላይ ለመጫወት ፈቃደኛ የሆኑትን “ቅልብና ተለጣፊ” እያሉ አመፀኞችንና ህግና ህገወጥነትን ቀላቅለው የሚጠቀሙትን "ህዝባዊና ሃገራዊ" እያሉ በማሽሟቀቅና በማሞገሥ አይሆንም፡፡

በአገራችን ከላይ የተጠቀሰውን አወንታዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ጠንካራ ፓርቲዎች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት የሚሆኑ ከኋላቀርነታችን ጋር የተያያዙቱ በርካታ ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው በምርጫ ዋዜማ ላይ ብቻ  ብቅ ብለው የሚጠፉ የመስቀል ወፍ ፓርቲዎች በሚሰጡት አፍራሽ መግለጫና አራጋቢ ጋዜጦችም አሉታዊ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑ እየታየ ነው፡፡ ተቃዋሚ መሆን ማለት መናድ ማፍረስ፣ በተገኘው አጋጣሚና ባመቸ ስልት በመጠቀም ማደናቀፍ ተደርጎ የሚወሰድበት ሁኔታ እንዲፈጠር እነዚህ ሃይሎች አሁንም እየሰሩ ስለመሆናቸው ከመግቢያው ጀምሮ ባየናቸው ሁነቶች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ነገር ግን ከላይ የተዘረዘሩት ነባራዊ ችግሮች እንደኛ ባሉ አገሮች ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊኖሩ እንደማይችሉ ወይም የዴሞክራሲ ስርዓት ሊገነባ እንደማይችል የሚያመላክቱ ሳይሆኑ ይልቁንም የነዚህ ነባራዊ ችግሮች መኖር ጠንካራ የፖለቲካ ፖርቲዎችን ለመፍጠርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት ከፍተኛ ትግልና ጥረት፤ ከፍተኛ ጥንቃቄና ብቃት ያለው የአፈፃፀም ስልት የሚጠይቅና ለዚህም የፖርቲዎችን የጋራ ምክር ቤት  ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ ፍንጭ የሚሰጥ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን ነው፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን የእነዚህና ለ3ኛ ጊዜ በተደጋጋሚ አጀንዳ ተጠምደው የውዝግብ መንገዶችን ለመክፈት የሚጥሩ ሃይሎችን በተመለከተ መንግስት መሰረታዊ የሆኑ አቅጣጫዎችን ተከትሎ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውን በጥንቃቄና በተስተካከለ አቅጣጫ ለመምራት የሚያደርገውን ርብርብ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት፣ህብረተሰቡም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተሟላ እውቀት እንዲኖረው ቢደረግና ለተቀመጠው አቅጣጫ ተግባራዊነት ሁሉም በየፊናው እንዲረባረብ ማድረግ እንዳለበት የሚያስጠነቅቅ ደወል ነው፡፡

እኚህ እንግዲህን ከብዙ በጥቂቱ መድረኩ 2002 እና የመድረኩ ዘማሪዎች እንደህብረት ደግሞ በምርጫ 97 ወቅት ብለው ብለው ያልተሳኩላቸው ፖለቲካዊ ኪሳራዎችና በመራራ ቋንቋ ቅርጫ ሆነው የከረሙባቸው ምክንያቶችና የማንነታቸው መገለጫዎች ናቸው፡፡

ስለሆነም ከላይ የተመለከቱ የመድረኩን የውድቀትና የመፈረካከስ ተጠየቆች ይዘን ዛሬ ደግሞ ልክ እንደተለመደውና ከላይ በተመለከተው አግባብ የዜሮ ድምር ፖለቲካ መድረኩን ላለፉት ሁለት ዓመታት ትተውት በውጭ የነበሩትና በውጭም ከስረው ሲያበቁ ተመልሰው ላለፉት 2 ዓመታቶች ሲተራመስና ሲከሳከስ የነበረውን መድረክ በሊቀመንበርነትና በውጭ ግንኙነት ሃላፊነት ይዘው ለመዘወር በዋዜማው የተከሰቱልን መራራና በየነ በበየነ "የምህዳር መጥበብ"ና በመራራ "ደርጉ ከኢህአዴግ ይሻላል" የቅርጫ ፖለቲካ ተጀምሯል፡፡

ለመሆኑ ዶ/ር መራራ እርሳቸውን እና ፓርቲያቸውን የተመለከቱ እና በጥቂቱ የተዘረዘሩ ከላይ የተመለከቱ ፖለቲካዊ ጉዶች ባሉበት ሁኔታ ኢህአዴግን ከደርግ ለማሳነስ ቢያንስ የደፈሩባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር ካደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ከጉዳያችን ጋር ተያያዥ የሆኑትን እየቆነጠርን በጥልቀት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ የምርጫ ሂደት ላይ ‹‹ምርጫ ›› እና ‹‹ቅርጫ›› በሚለው አባባላቸው የሚታወቁትን ዶ/ር መራራ ጋዜጣዋ ያነሳችላቸው የመጀመሪያ ትያቄ የምርጫና ቅርጫን ትርጉም የተመለከተ ነው፡፡

እርሳቸውም በሃገራችን ባህል በበዓላት ማህበረሰቡ በቡድን ገዝቶት የሚከፋፈለውን የእርድ ሥርዓት መነሻ በማድረግ እና ከኢትዮጵያ የምርጫ ሂደት ጋር በማያያዝ ከቅርጫው ደንብና ሥርዓት ባፈነገጠ መልክ ወይም ደግሞ የህዝብ ድምጽ ልክ እንደ ቅርጫው መከፋፈል አለበት በሚል የስልጣን ጥማቸው መነሻነት ከላይ በተመለከተው የምርጫ 2002 እና 97 ትዝታችን አግባብ ኢህአዴግ ሁሉንም ጠቅልሎ ይወስዳል የሚል ይዘት ያለው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ያም ሆኖ ግን ለአባባላቸው የሰጡት ትርጓሜ በራሱ የሰውየውን የሥልጣን ጥምና በመሰረቱም ከመድብለ ፓርቲ ጋር በሚቃረን አግባብ የእንከፋፈለው አባዜያቸው የተረጋገጠበት ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ይህ አስተሳሰባቸው አስቀድሞም የነበረና በመሰረቱ የምርጫን አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባና ጸረ ዲሞክራሲያዊ አመላከከት በመሆኑ ነው፡፡

በህዝብ ስም ስለህዝብ ስለ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚናገር ሰው መልሶ ምርጫን ከቅርጫ ጋር ማያያዝ ተገቢነት የሌለው ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ፍጹም ሚጣረስ አስተሳሰብ ነው፡፡ እንከፋፈለው ብሎ ነገር አስቀድሞ የህዘብ ይሁንታ የሌለበትና የህዝብን ፈቃድ ያላገኘ ሥልጣን ነው የሚሆነው፡፡ እንከፋፈለው ከተባለ ደግሞ የምርጫ ሥርዓት አስቀድሞ ነገር የማያሻንና ልክ እንደደርጉ እዛው መደላደልና በአዋጅ ማስነገር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጸረ ዴሞክራሲያዊና ፍጹም አምባገናናዊነት ነው፡፡ስለሆነም ድምጽ ያለህዝቡ በጎ ፈቃድ ሲከፋፈል በተጫባጭ የምናውቀውና በቅርጫ መልክ የሚከፋፈለው ደርግ ነበርና ያለፈውን ሥርዓት ናፋቂ የሚባሉት እነ ዶ/ር መራረና ፕ/ር በየነ ለዚሁና ያለፈውን ሥርዓት ስለመናፈቃቸው ይኸው እነርሱ በመሰከሩትና ከላይ በተመለከተው የናፍቆት አመለካከታቸው ምክንያት ነው፡፡

ዶ/ር መራራ በመጽሃፋቸው ላይ ‹‹ በአፍሪካ ሃገር የመንግስት ጥያቄ የአቅም ጥያቄ ነው›› ሲሉ ያሰፈሩትንም ነጥብ ትርጓሜ በተመለከተ ከጋዜጣው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ ልክ ከላይ በተመለከተው አግባብ ደርግን መናፈቃቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይኸውም በምርጫ የሚሳተፉት ወታደራዊ አቅም ስለሌላቸው መሆኑን የጠቀሱበት አግባብ ነው፡፡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እተጋለሁ የሚል ፓርቲና የፖለቲካ ድርጅት ሲጀመር ሥልጣን ለመያዝ የሚያስችለው ምርጫና ምርጫ እንጂ ሌላ ነገር እንደሌለ እና ሊኖርም እንደማይገባው ከሰመረቱ ከማመንና በተግባርም በዚሁ በመገለጥ መጀመር ግድ ይለዋል፡፡

ዶ/ር መራራ ግን ሥለ ዴሞክራሲ ያወራሉ እንጂ በተግባርና በተጨባጭ በትዝታችንም እንዳየነው ሆነ አሁን ምርጫ 2007ን ታሳቢ አድረገው ለሡንደቅ በሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ ከላይ በተመለከተው አግባብ ያረጋገጡልን መድረኩ ወታደራዊ አቅም ኖሮት ቢሆን ኖሮ በምርጫ የማይወዳደርና በአፈሙዝ ሥልጣን ለመያዝ የሚፈልግ መሆኑን ነው፡፡

ይህን በሌላ አግባብ እንድናየው ካስፈለገን ደግሞ መንግስት የሚመራው በኢህአዴግ ነውና ወታደራዊ አቅሙን ተጠቅሞ ምርጫ እንኳንስ ምህዳር ምናምን ወላ ሰፋ ጠበበ፤ ምርጫም የሚባል ሥርዓት ባያሰፍን እነ መድረክን ሊያንጫጫ ባለተገባ ነበር እንደማለት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ወታደራዊ አቅም ቢኖረውም ስለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለው አቋምና ከላይ በተመለከቱ የአፈጣጠሩ ምክንያቶች ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት እየተጋ መገኘቱ በአንጻሩ ደግሞ ሥልጣንን ከወታደራዊ አቅም አንጻር የሚተረጉሙት እነ ዶ/ር

መራራ ሚናቸው ከደርግ የከፉ እና የባሱ ሥለመሆናቸው መልሱን ከመነሻው እያገኘን ይመስላል፡፡

ዶ/ር መራራ ይልቁንም ከደርግ መባሳቸውን እና ስለ ዜሮ ድምር ፖለቲካ ግራ በመጋባት ግራ ሊያጋቡ የሻቱበት ሚስጢር ደግሞ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ትብብር ጋር ተያይዞ ስለ ምርጫ 2007 ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ በመሆኑ በክፍል ሁለት ትርክታችን ሳንቆነጥር እንደወረደ ተመልክተን ልናሄሰው እንገደዳለን፡፡